# ዋሽንግተን ዲሲ የእሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ

## የእሳት መከላከል ክፍል – ጠቅላይ እዝ

| **ርእሰ-ጉዳይ: ፍንዳታ እና ፈንጂዎች** | **ጠቅላይ እዝ:** 615 |
|---|---|
| **ክፍል: የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት** | **የወጣበት ቀን:** ጥቅምት 1, 2009 |
| **ባለስልጣን:** **DCMR 12, ምዕራፍ 12H, ክፍል F-107H**<br>**የእሳት መከላከል ደንብ ማጠናከሪያ** | **አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን:** እስከ ሚወገድ ድረስ |

## I. አድማስ

በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኘው መረጃ ለሁሉም ከዲሲ እሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ የእሳት መከላከል ክፍል የፍንዳታ እና ፈንጂዎች ፈቃዶች ለማግኘት የሚጠይቁ አመልካቾች ያገለግላል።

## II. አላማ

የዚህ ጠቅላይ እዝ አላማ ፍንዳታዎችን እና ፈንጂዎችን የመጠቀም ጥያቄዎች አቀባበል እና ክንውን ሂደት ደረጃው የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው።

## III. የቃላት ፍች

የለም

## IV. ፖሊሲ

በአንድ በኩል የፍንዳታዎች እና ፈንጂዎች የመጠቀም ጥያቄዎች ብቁ እና ስርአት ባለው አካሄድ እንዲሁም ያለምንም መዘግየት ማከናወን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የህብረተሰቡን፣ የአከናዋኞችን፣ እና የተቆጣጣሪዎችን ደህንነት ማረጋገጥ እንዲሁም ህጎችን፣ ደንቦችን እና ስነስርአቶችን አክብሮ መስራት የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት ፖሊሲ ነው።

## V. አሰራር

የፍንዳታዎች ፈቃድ ወይንም ፈንጂዎችን የማጓጓዝ ፈቃድ የሚጠይቁ አመልካቾች ማመልከቻዎቹ ከመጽደቃቸው በፊት የግድ የሚከተሉትን ነገሮች ማቅረብ አለባቸው:

1. የ DCRA ማመልከቻ ለ “የግል ይዞታ ላይ የሚደረግ ግንባታ።”

2. ሁሉም የተሞሉ የፈቃድ ማመልከቻዎች እና ለዲሲ ግምጃቤት ተከፋይ የሚሆኑ ትክክለኛ መጠን የያዙ የቼክ ወይንም የገንዘብ ትእዛዞች ወደ የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት በአካል በመሄድ ማስረከብ የግድ ይላል: (ማስታወሻ: ማመልከቻው በእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት እና ኦንላይን ላይ ይገኛል)።

3. የተሽከርካሪ መረጃ (የምዝገባ እና ታርጋ ቁጥር፣ ቀለም፣ ብራንድ፣ ሞዴል፣ እና ዓመተ ምህረት)

4. የፈንጂዎቹ አይነት እና ጥራት፣ ፈንጂዎቹ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ቦታ፣ ፈንጂዎቹ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚጓጓዙበት መንገድ (በእሳት ማርሻሉ በጸደቀው መሰረት) የትኛው መሆኑ፣ እቃው የሚጓዝባቸው/የሚንቀሳቀስባቸው ጊዜያት፣ እና ፍንዳታው የሚካሄድበትን የጊዜ ሰሌዳ የሚያሳዩ የጽሑፍ ሰነዶች። **ማስታወሻ:** ይህ መረጃ የሚያዘውበሚስጥር ነው።

5. ትክክለኛ የመድህን ሰነዶች

6. አመልካቹ ፈንጂዎችን እንዲይዝ እና እንዲጠቀም የሚያስችሉት የግዛት እና የፌደራል ፈቃዶች ቅጂዎች (ዕድሜያቸው የግድ ቢያንስ 21 አመት የሞላቸው መሆን አለበት)።

7. አመልካቹ ፈንጂዎችን እንዲይዝ እና እንዲጠቀም የሚያስችሉት ፈቃዶች ቅጂዎች (ዕድሜያቸው የግድ ቢያንስ 21 አመት የሞላቸው መሆን አለበት)።

<u>**ጠቃሚ የፍንዳታ እና ፈንጂዎች ተጨማሪ መረጃ**</u>

1. በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የፍንዳታ ስራዎች ሲያከናውኑ የሚከተለው ቦታ እና ነገሮችን ለመጠቀም የእሳት መምሪያውን ፈቃድ ማግኘት ይኖርብዎታል:

   ሀ. ፍንዳታው የሚከናወንበት ቦታ
   ለ. ፈንጂዎቹን የጫነው ተሽከርካሪ
   ሐ. የፍንዳታዎቹ ማቀጣጠያ የጫነ ተሽከርካሪ

2. ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ነገሮች በ NFPA 495 መሰረት እየሄዱ መሆናቸው ለማረጋገጥ፣ አስቀድሞ በተለየው ቦታ፣ ቀን፣ እና ሰአት በዲሲ የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት ሀዝማት ፍተሻዎች ቅርኝጫፍ አማካኝነት የተሽከርካሪ ደህንነት ፍተሻ መከናወን አለበት። ይህ ፍተሻ ብዙጊዜ የሚሰጠው በ 4600 Shepherd Parkway SW ላይ በሚገኘው የዲሲ እሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ የስልጠና አካዳሚ ጊቢ ውስጥ ነው።

3. ፈቃዶች (የተሽከርካሪ እና የቦታ) አገልግሎት የሚሰጡት ለ 45 የስራ ቀናቶች ብቻ ሲሆን አገልግሎታቸው ከማብቃቱ ቢያንስ ከ 72 ሰዓታት በፊት መታደስ ይኖርባቸዋል።

4. ሁሉም የፈንጂዎች እና የፍንዳታዎች ማጓጓዣ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ፈንጂዎቹ በሚጓጓዙበት ጊዜ ከዲሲ ግዛት ተነስተው የተፈቀደላቸው ቦታ ላይ እስኪደርሱ ድረስ በሚመለከተው ባለስልጣን ታጅበው ይጓዛሉ።

   ሀ. በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሕግ ሆኖ የጸደቀው የ 2006 የአለማቀፍ የእሳት ደንብ ክፍል 3301.5 (ቁጥጥር) እንደሚደነግገው፣ የደንቡ አስፈጻሚ አካል (የእሳት ማርሻል) ክንዋኔዎች የደህንነት እና እሳት ደንቦችን ባከበረ መልኩ እየተካሄዱ መሆናቸው ለማረጋገጥ በማናቸውም ጊዜ የቁጥጥር ስራ የመስራት ስልጣን አለው።

ማሳሰቢያ: ሁሉም ከፍንዳታዎች እና ፈንጂዎች የተያያዙ ጥያቄዎች ወደሚከተለው አካል መቅረብ አለባቸው:

**District of Columbia**
**Fire & Emergency Medical Services Department**
**Fire Prevention Division**
**1100 4th Street SW Suite E700**
**Washington, DC 20024**
**(202) 727-1614**